

## 29-2

# ለሚበሳጭ እግዚአብሔር መልስ አለው

### 2) ከእግዚአብሔር ጋር ያለው አንድነት ሲደፈርስ

*"የእግዚአብሔር መንፈስ ከሳኦል ራቀ"* (1 ሳሙ. 16፥14) ይላል። የእግዚአብሔር መንፈስ ከሳኦል የራቀበት ምክንያት፥ እግዚአብሔር ሳኦልን በሁለት ነገር ስላዘንበት ነበር።

1ኛው፥ ንጉሥ ሳኦል ሳሙኤልን በጊልገላ ሲጠብቀው ሳሙኤል ቶሎ ሳይመጣ ቀረ። ሳሙኤል አለመምጣቱን ሲያይ መታገስ አቅቶት ሳኦል *"የሚቃጠለውን መሥዋዕትና የደኅንነት መሥዋዕት አምጡልኝ አለ። የሚቃጠለውንም መሥዋዕት አሳረገ"* ይላል 1ኛ ሳሙኤል 13፥9። እግዚአብሔር የደነገገው ሕግ መስዋዕት ለእግዚአብሔር ማቅረብ የሚችለው ከለዋ ነገድ የሆነ ሰው ብቻ ነበር። ሳኦል ግን ከቢንያም ነገድ እንጂ ሌዋዊ አለነበረም። ሳኦል ሌዋዊ ባለመሆኑ መስዋዕት እንዲያቀርብ ያልተፈቀደለት መሆኑን በደንብ ያውቃል። ይሁን እንጂ በድፍረቱ የእግዚአብሔርን ትዕዛዝ በመናቅና በማቃለል ማድረግ የማይገባውን ነገር አደረገ። ሳሙኤል ከሥፍራው ደርሶ ሳኦል ያደርገውን ሲያይ፥ *"አላበጀህም፤ አምላክህ እግዚአብሄር ያዘዘህን ትዕዛዝ አልጠበቅህም፤ ዛሬ እግዚአብሔር መንግሥትህን በእሥራኤል ላይ ለዘላለም አጽንቶልህ ነበር። አሁንም መንግሥትህ አይጸናም፤ እግዚአብሔር እንደልቡ የሆነ ሰው መርጦአል፤ እግዚአብሔር ያዘዘህን አልጠበቅህምና እግዚአብሔር በሕዝቡ ላይ አለቃ ይሆን ዘንድ አዝዞታል አለው"* (1ኛ ሳሙኤል 13፥13-14)።

2ኛ. እግዚአብሔር አማሌቃውያንን ድል ሲያደርግ እንስሳም ሆነ ሰው አንድም ሳያስቀር በሙሉ እንዲያጠፋ ሳኦልን ነግሮት ነበር። ሳኦል ግን አማሌቃውያንን ድል ካደርገ በኋላ የአማሌቃውያንን ንጉሥ፥ አጋግን መግደል ሲገባው ማርኮ በሕይወት አቆየው። ሳኦል ይህን ያደርገው ምናልባት ከጦርነት በድል አድራጊነት በሕዝቡ መካከል ሲያልፍ ማርኮ የያዘውን አጋግን ለሕዝቡ ለማሳየት ፈልጎ ይሆናል። እየደጋገመ ሆን ብሎ የእግዚአብሔርን ትዕዛዝ የሚጥሰውን ሰው እግዚአብሔር ሊገለገልበት የማይችል በመሆኑ፥ የእግዚአብሔር መንፈስ ከሳኦል ራቀ። በዚህ ምክንያት ሳኦል ትልቅ የመንፈሳዊ ችግር እንደደረሰበት እንገነዘባለን። ሳኦል ከእግዚአብሔር ጋር የተቀራረበ ኅብረት ስላልነበረው በእግዚአብሔር ውስጥ በመሆን የሚገኘውን ሰላም፣ ዕረፍትና ጸጥታ አያውቅም ነበር። ስለዚህ ሳኦል የመረበሹና እረፍት የማጣቱ ዋናው ምክንያት ይሄ ነበር።

የሳኦል መረበሽ ምክንያት የሥጋ ፍሬ ውጤት እንጂ የመንፈስ ፍሬ አልነበረም። የመንፈስ ፍሬ ጸጥታ፣ ሰላምና እረፍት ነው። የእግዚአብሔር መንፈስ በማንም ላይ ሁከትና መረበሽ አያመጣም። ባለመታዘዙ ምክንያት በሥጋ የሚመራ አማኝ ሁከትና ረብሻ በሕይወቱ እንዲደርስ ያደርጋል። ሕይወቱን መንፈስ ቅዱስ የሚገዛው ከሆነ፥ የክርስቶስ ሰላምና ጸጥታ የሞላው ይሆናል። በሳኦል ሕይወት ያየነው ዓይነት ሁካትና ረብሻ ሊደርስ የሚችለው ከእግዚአብሔር ፈቃድና ክልል ውጪ በሚኖረው ሰው ላይ ብቻ ነው። ኃጢአት በሰው ሕይወት ውስጥ ሁከትና ረብሻ የሚፈጥር ከሆነ መፍትሄ አለው። መፍትሄውም በ1ኛ ዮሐንስ 1፥9 ላይ ተጽፏል። *"ኃጢአታችን ብንናዘዝ ኃጢአታችንን ይቅር ሊለን ከዓመጻም ሁሉ ሊያነጻን የታመነና ጻድቅ ነው"* የሚለው ነው። ሳኦል በንስሃ ወደ እግዚአብሔር ቢጮህ ኖሮ፥ ይቅርታንና መታደስን ከእግዚአብሔር ይቀበል ነበር። ሳኦል ኃጢአት እንደሠራው ሁሉ፥ ዳዊትም በኃጢአት ተላልፎአል።

እንዲያውም ብዙዎቻችን የዳዊት ኃጢአት ከሳኦል የከፋ ነበር ማለታችን አይቀርም። ትክክልም ነው። ትልቁ ልዩነታቸው፥ ዳዊት ኃጢአቱ አስለቅሶታል። ባደረገው በደል ተጸጽቷል። ወደ እግዚአብሔርም *"በሂሶጵ እርጨኝ፤ እነጻማለሁ፤ እጠበኝ፤ ከበረዶም ይልቅ ነጭ እሆናለሁ"* (መዝ. 51፥7) ብሎ ጮኾኣል። ከእግዚአብሔር ጋር ያለንን ግንኙነት በማበላሸት ምክንያት ለሚደርስብን መረበሽና ሰላም ማጣት ዋና መድኃኒቱ የተደበቀውን ኃጢአታችንን መናዘዝ ብቻ ነው።

**3ኛ. የሥጋ ፍሬ ሲያብብ**

ሳኦል የተረበሸበት ሰላም ያጣበት ሦስተኛው ምክንያት የሥጋ ፍሬ በሕይወቱ በመብቀሉ ነው። ለአዕምሮው መረበሽ መድኃኒት እንዲሆንለት አማካሪዎቹ ያገኙለት ዳዊት በገና እይተጫወተ የደከመ ሥጋውን እንዲያዝናናለት፣ የረበሸውን መንፈሱን ጸጥ እንዲያደርግለት ነበር። *"ከዚያም ጊዜ ጀምሮ ከእግዚአብሔር የተላከ ክፉ መንፈስ በሳኦል ላይ በሚመጣበት ጊዜ ሁሉ ዳዊት በገናውን አንሥቶ ይደረድራል፤ ክፉውም መንፈስ ለቅቆት ስለሚሄድ ሳኦል እየተሻለው እንደገና ጤናማ ይሆናል"* (1ኛ ሳሙ. 16፥23)። ሳኦል ዳዊትን አጠገቡ ቆሞ በገና ሲጫወትለት በጣም ስለ ወደደው ጋሻ ጃግሬው አደረገው። ዳዊትም ለሳኦል የአዕምሮ መረበሽ መድኃኒት ሆነ። ይሁን እንጂ ሳኦል ዳዊትን ለመግደል ብዙ ጊዜ ሙከራ አድርጓል። በዚህም በእርሱና በዳዊት መካከል በነበረው ፍቅርና አንድነት ላይ አመጽ ሠራ። ፍቅር የመንፈስ ቅዱስ ፍሬ ሲሆን፥ ፍቅር የሌለበት ሕይወት ግን የሥጋ ፍሬ ውጤት ነው። ሃዋርያው ጳውሎስ የእግዚአብሔር ልጅ በሆነው አማኝ ሕይወት ውስጥ በመንፈስ ቅዱስ አማካኝነት ፍቅር ሲፈስ ምን ዓይነት ውጤት እንደሚታይ ለቆሮንቶስ ምዕመናን በጻፈው መልዕክቱ ይዘረዝራል። ፍቅር ስንል በዓለም የምናየውን ዓይነት ፍቅር ማለታችን አይደለም። በአማኝ ሕይወት ውስጥ መንፈስ ቅዱስ ሲያድርበት የሚኖረውን መንፈሳዊ ፍቅር ማለታችን ነው። "ፍቅር ይታገሳል" (1 ቆሮ 13፥4) ይላል። ይህም ማለት ቶሎ ቱግ አይልም፣ አይበሳጭም ማለቱ ነው። ፍቅር ሩህሩህ እንጂ ጨካኝ አይደለም። ፍቅር አይቀናም። ፍቅር የራሱን ጥቅም ብቻ አይፈልግም። ፍቅር በራሱ አይኩራራም።

ብዙዎቻችን በቀላሉ ብስጭት የምንለው በምን ምክንያት ይሆን? የራሳችን ጥቅም ተነካብን፣ ሌሎች ልናደርገው የምንፈልገውን ዓላማችንና ዕቅዳችንን አቃወሱብን ብለን ነው። ወይንም እኛ እንሠራዋለን ብለን ያቀድናቸውን ሃሳቦች እኛ በሥራ ላይ ሳናውልወ ቀድመውን አደረጉት በማለት ነው። ብዙ ጊዜ "እኔ! እኔ" የሚል መንፈስ ሲያጠቃን በሌላ አነጋገር እራሳችንን የሁሉ ነገር መካከላዊ ወይንም ቁንጮ ስናደርግ ሌሎች እኛ ከምንፈልገው ዓላማ ውጪ ሲያደርጉ ስናይ በቀላሉ ብስጩ እንሆናለን። የእኛ ፍላጎት ከሌሎች ሰዎች በፊት ካልተሟል ትንሽ ነገር እንኳን በቀላሉ ይቆረቁረናል። ለዚህ ነው ጳውሎስ "ፍቅር የራሱን ጥቅም ብቻ አይፈልግም" ያለው። "ፍቅር አይኮራም" ሲል ከሁሉም እበልጣለሁ ብሎ አያስብም ማለቱ ነው። ብዙ ጊዜ በቀላሉ ቅር የምንሰኘው፣ የምንበሳጨው፣ ሰዎች የሚገባንን ክብርና ደረጃ የከለከሉን ወይንም አሳንሰው ያዩን ስለሚመስለን ነው። ፍቅር የራሱን አይፈልግም። የሚገባኝን ክብር ተነፈግሁ በማለት አይበሳጭም፤ የሌላውን ሰው መንፈስ በቀላሉ አይጠራጠርም። ብስጩነት የሥጋ ፍሬ ውጤት ነው። መንፈስ ቅዱስ በአማኝ ሕይወት ውስጥ ተወዳጅነትን የሚፈጥር ሲሆን፥ የሥጋ መንፈስ ግን በቀላሉ መበሳጨትን፣ ከሰው ጋር በአግባብ መኖር አለመቻለን፣ አለመውደድን ያመጣል። ሳኦል በቀላሉ በመበሳጨቱ ዳዊት ለእርሱ የነበረውን ፍቅር ወይንም እርሱ ለዳዊት የነበረውን ፍቅር ያቀዘቅዝ ነበር። በወንድሞቻችን ወይንም በእህቶቻችን ላይ ተበሳጭተን የምናሳየው መጥፎ ስሜትና መንፈስ የሥጋ ፍሬ ውጤት ሲሆን፥ በዚህ ምክንያት የክርስቶስ ውብ የሆነ ቁንጅናና መልካም ባህርይ በሕይወታችን እንዳይታይ ያደርጋል። በዚህ ፈንታ ግን ጠላታችን ዲያብሎስ የምናደርገውን መቆጣጠሩ ብቻ ሳይሆን፥ በምላሳችንም ሆነ በተግባራችን የእርሱን ዓላማ የምንፈጽም ተባባሪዎቹ ያደርገናል። ሳኦል በመልካም ጀምሮ በመጥፎ የጨረሰ አስቸጋሪና መጥፎ ሰው ነበር። የአማኝን ሕይወት መንፈስ ቅዱስ ዕለታዊ ሕይወቱን ካልተቆጣጠረው በጥሩ ቢጀምርም እንኳን በጥሩ ለመጨረሱ ማስተማመኛ የለውም።

**አጠቃላይ ሃሳብ**

ሳኦል በወቅቱ የሥጋና የመንፈስ እርፍት ያስፈልገው ነበር። የችግሩ ምክንያት አንዱ ይሄ ነበር። ይሁን እንጂ በወቅቱ ያጋጠመውን ችግር ለማቃለል ሲሯሯጥ ነፍሱ ይበልጥ ታወከች። ይህን ዓይነት ችግር የሚታየው በሳኦል ሕይወት ብቻ ሳይሆን በእኛም ሕይወት ይታያል። በአጭር ጊዜ ብዙ ነገር ለማገባደድ፣ ብዙ ስለምንሮጥ ለሥጋችን ተፈላጊውን እረፍት መስጠት ያቅተናል። በዚህ ምክንያት በቀላሉ ብስጩዎች እንሆናለን። እኛ በውስጡ ስላለን ብዙ ጊዜ የተለወጠውን ባሕሪ ያችንን ማየት አንችልም። በአካባቢያችን ያሉ አብረውን የሚኖሩ ግን የባህሪያችንን ለውጥ በቀላሉ ማየት ይችላሉ። ችግሩ በእኛ ላይ ብቻ ተወስኖ የሚቀር አይደለም። አብረውን ለሚኖሩ ሰዎች በጣም አስቸጋሪዎች እንሆናለን። የማያበሳጨው፣ ትንሹና ቀላሉ ነገር እንድንበሳጭ ያደርገናል። በእውነትና በጥሩ መንፈስ የተነገረውን የሌላውን ሰው ንግግር ወይን አስተያየት በትክክል በመመልከት ፈንታ በተቃራኒ እንዲገባን ይሆናል። እንዲሁም ያለአንዳች ምክንያት ተጠራጣሪዎች እንሆናል።

የችግራችን ሁሉ ምክንያት ሌሎች እንደሆኑ ከመመልከት ይልቅ፥ ረጋ ብለን እራሳችንን እንጠይቅ። የሥጋ ድካም የእንቅልፍ ማጣት ይኖርብን ይሆን? አንዳንዶቻችን ጥሩ እንቅልፍ ከተኛን ብዙ ጊዜያችን ይሆናል። በተለይ በውጪ አገር የምንኖር ሥራችን አድካሚና የሚያሯሩጥ በመሆኑ ሥጋችን ከመጠን በላይ ይደከማል። የአለችንን አጭር የዕረፍት ጊዜ እንኳን በአግባቡ አንጠቀምበትም። በዚህ ምክንያት በቀላሉ ስለምንበሳጭ የክርስቲያን ባህሪ በሕይወታችን እንዲታይ አናደርግም። ከአማኝ የማይጠበቀውን ዓይነት ባህሪ በማሳየታችን አብረውን የሚኖሩ “ክርስትና እንደ እከሌ ከሆነ፥ በአፍንጫዬ ይውጣ” እንዲሉ እናደርጋቸዋለን። በዚህም ምክንያት ለጌታ መልካም ምስክሮች አንሆንም። ስለዚህ ለሥጋችን ተፈላጊውን እረፍት አንንፈገው። እረፍት ስል እንዛግ ማለቴ አይደለም። ወይንም ስነፎች በእረፍት አማካኝተን ሥራ እንደ ጦር የምንሸሽ እንሁን ማለቴ አይደለም። አብዝተን ካረፍንና አዕምሮአችን ሥራ ከፈታ ደግሞ ሳይጣን አዕምሮአችንን የእርሱ ኳስ መጫወቻ ሜዳ እንዲሆን መፍቀዳችን ይሆናል።

ሥጋችን በቂ እረፍት ቢያገኝም፣ በቀላሉ የምንበሳጭ አብረውን ለሚኖሩ ሰላም የማንሰጥ ከሆነ፥ ወደ ውስጥ ጠልቅ ብለን ሕይወታችንን መመርመር ይገባናል። ከእግዚአብሔር ጋር ያለን ግንኙነት ምን ያህል የተቀራረበ እንደሆነ እራሳችንን እንጠይቅ። የብስጩነታችን ምክንያት ምናልባት ከአምላካችን ጋር ያለን ግንኙነት የሻከረ በመሆኑ ሊሆን ይችላል። ይህ ከሆነ የመንፈስ ቅዱስ ፍሬ በሕይወታችን አብቦ በመታየት ፈንታ የሥጋ ፍሬ በሕይወታችን ሞልቶ እንዲታይ ይሆናል። የሥጋ ፍሬ በሕይወታችን መብቀሉን ለማየት ይህን ያህል አስቸጋሪ አይደለም። ሥጋ ሁልጊዜ ራሱን ያስቀድማል። የራሱን ጥቅም እንጂ የሌላው ሰው መጎዳት የሌላው ሰው ፍላጎት ጨርሶ አይታየውም። የእርሱ ፍላጎት ከሌላው ሰው ፍላጎት ቀድሞ ካልተሟላ በቀላሉ ይበሳጫል። በፍቅር ፈንታ ጥላቻ ሕይወቱን ይሞላዋል።

ችግራችን ከላይ እንደገለጽነው ከአምላካችን ጋር የቀረበ ግንኙነት በማጣትና ኃጢአት በሕይወታችን እየሰለጠነ መሆኑን ስንረዳ ሁኔታችንን ዝም ብለን ከመመልከት ይልቅ በቶሎ አንድ ነገር ማድረግ ይገባናል። በመጀመሪያ ደረጃ በንስሃ ወደ እግዚአብሔር ቀርበን ድካማችንንና መተላለፋችንን መግለጽ ይገባናል። *“ኃጢአታችንን ለእግዚአብሔር ብንናዘዝ እርሱ ታማኝና ጻድቅ ስለሆነ ኃጢአታችንን ሁሉ ይቅር ይለናል፤ ከበደላችንም ሁሉ ያነጻናል”* (1ኛ ዮሐ. 1፥9) ይላል። የፍቅር ሰዎች መሆን እንዳለብን መርሳት የለብንም። ክርስቶስ እርስ በርሳችን እንድንዋደድ አዝዞናል። በውስጣችን ፍቅር በማጣት ምክንያት በቀላሉ በሌላው ላይ የምንበሳጭና በውስጣችን እረፍተ ቢስ እንድንሆን የሚያደርገን ከሆነ ችግራችን መፈሳዊ ስለሆነ ሕይወታችን መታረም የሚገባው ነው። ፍቅር በመንፈስ ቅዱስ አማካኝነት በልባችን ፈስሶ የክርስቶስ ባህሪ በሕይወታችን እንዲታይ እንዲያደርግ መንፈስ ቅዱስን ወደ ልባችን እንጋብዘው። ያኔ ለሰው ሁሉ እውነተኛና ያልተበረዘ ፍቅር ይታይብናል። የእኔ ፍላጎት ከሁሉ ሰው በፊት ለምን አልተሟላም በማለት በራሳችንና በሌሎች አንበሳጭ።

……………………………………………………………………